# የፍትህ ዘርፉ ተግዳራቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች!

ክፍል ሁለትና የመጨረሻ

**ተስፋዬ ለማ** 03/0/314

አገር አቀፍ የፍትህና የመልካም አስተዳደር መድረክ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት የተውጣጡና አስፈጻሚ አካላት በተገኙበት በሴክተሩ የተለዩ ተግዳራቶችና የችግሮቹ መንስኤዎች ላይ ውይይት መደረጉንና ይህ የውጥን ችግር ነቅሶ አውጥቶ ለመፍታት የሚደረገው አካሄድ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ዓይነተኛ አጋጣሚ እንደነበር በውይይት መዳበሩ በክፍል አንድ ተገልጾ ነበር።

ሪፖርቱ እንደቀረበና ውይይት እንደተደረገበት በመጠቆምም እቅዱ የያዛቸው የመፍትሄ ሃሳቦችና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን በዚህ ክፍል ለማቅረብ መጠቆማችን ይታወቃል። ተነቅሰው ከወጡት ተግዳራቶቹ በመነሳት በጥናት ላይ ተደግፎ የፍትህ ሴክተሩ በቀጣይ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችለውን እቅድ ቀርቦ ውይይት መደረጉን ለማየት ተሞክሮ ነበር።

በምክክር መድረኩ የግልጽነትና ተጠያቂነትን አለመስፈን አንዱ ማነቆ እንደነበር ለማየት ተችሏል። ይህ ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ መሠረታዊ ከሆኑ መርሆዎች መካከል ወሣኝ መሆኑን ተመልክቷል። በዚህ ምክንያት በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ ሙያተኞችና የድጋፍ ሠራተኞች ለነዋሪው ሕዝብ ግልፅና ተጠያቂ የሚሆኑበትን አሠራር መዘርጋትና መፈፀም እንዳለበትም በእቅዱ ተካቷል።

በፍትህ ሴክተሩ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የፍትህ አካላት ለህዝቡ አሊያም ለሚመለከታቸው ተቋማት ተጠያቂ መሆን ይኖርባቸዋል። ለብልሹ አሠራር መንገድ ሲከፍቱና ሲያጠፉም በሕግ የሚታረሙበትን ሥርዓት በመተግበር

በኃላፊነት ስሜት እንዲንቀሳቀሱ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም እቅዱ ያመላክታል።

ግልፅ የሆነ የአሠራር ሥርዓትን መዘርጋት ሕብረተሰቡ መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ ያግዘዋል። ማግኘት የሚገባውን አገልግሎት ለይቶ ያውቃል። ያንን አገልግሎት በተገቢው መንገድ ካላገኘ ለሚመለከተው ክፍል ለምን የሚል ጥያቄ ያነሳል።

ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ከማቅረብ አልፎ አገልግሎቱን ማግኘት መብቱ ሆኖ እያለ ያንን ለማግኘት ሲል አስፈላጊ ያልሆነ ነገር አያደርግም። አገልግሎቱን በነጻ ባለማግኘቱ ተቆጭቶ ብልሹ አሠራርን ይዋጋል። በነጻ ማግኘት ለሚኖርበት አገልግሎት ተገቢነት የሌለውን ወጪ ከማውጣት ይቆጠባል። ይህ ደግሞ የኪራይ ሰብሳቢነትን ትግል ያጠናክራል።

ግልጽነትን ማስፈን ሲባል ሕብረተሰቡ እቅዶችንና አፈጻጸማቸውን፣ የእያንዳንዱ አገልግሎት አሰጣጥና ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ምን ምን እንደሆኑ፣ አንድን አገልግሎት ለማግኘት ዜጎች በቅድሚያ ማሟላት ያለባቸውን ነገር ለይቶ ማቅረብ፣ ሕብረተሰቡ በዘርፉ ለመፈጸም የሚዘጋጁ እቅዶችን ገምግሞ እንዲያጸድቅ ማድረግ፣ ያጸደቃቸውን እቅዶች አፈጻጸም በመከታተልና በመገምገም ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርግ አሰራር መዘርጋት፣ ይህ በቀጣይ መደረግ እንዳለበትም በአገር አቀፍ የፍትህና መልካም አስተዳደር ማሻሻያ እቅድ በጉልህ ተመልክቷል።

ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት የህዝብ ነቀርሳ የእድገት ፀር ነው። ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት በተንሰራፋባት አገር ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ይቻላል ተብሎ አይታሰብም። ልማትን የሚያደናቅፍና የህዝቦችን ዴሞክራሲያዊና ተፈጥሯዊ መብቶችን የሚደፈጥጥ ነው።

ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት ድህነትንና ጉስቁልናን የሚያስፋፋና የሚያባብስ  ወደር የለሽ የህዝብ እድገት ጠላት መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አንጻር ሙስናንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት የመጀመሪያው እርምጃ መከላከል መሆኑ እሙን ነው። በመሆኑም ለብልሹ አሠራሮችና ለሙስና የሚዳርጉ የአሠራርና የሕግ ክፍተቶችን መለየትና መዝጋት ቀዳሚ ተግባር መሆኑን በእቅዱ ተለይቶ ቀርቧል።

ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት በልማታዊ አስተሳሰብ ካልተመታ ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ አይቻልም። ልማታዊነት እየተጠናከረና የህዝቡ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እየጎለበተ ሊሄድ የሚችለው ደግሞ ሕዝቡ ልማቱ የራሱ መሆኑን በመገንዘብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ሲችል እንደሆነ ይታወቃል። ያለ ህዝብ ተሳትፎ እድገት ሊመጣ ስለማይችል ህዝቡ የእድገቱ ተዋናይ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚህም ጋር ሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣኑን በተገቢው መንገድ መጠቀም ሲችል ብሎም  የማስተማር፣ የማረም፣ ለሕግ የማቅረብ ሥልጣኑን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ሲፈጠርለት እንደሆነ እሙን ነው። ሕብረተሰቡ ብልሹ አሠራሮችን እየተቆጣጠረ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ እንዲችል አስተማማኝ የሕግ ከለላና ጥበቃ በመንግሥት በኩል እንደሚደረግለት ተጨባጭ ነገር ማሳየት ይፈልጋል። ይህንን በግልጽ ማሳየት የሚችል ቀላል፣ ያልተወሳሰበና በቀላሉ ሊረዳውና ሊፈጽመው የሚችል አሠራርን መዘርጋትም የወጣው  የእቅዱ አካል ሆኗል።

አመራሮችና በዘርፉ የሚሰሩ ሙያተኞች ሕብረተሰቡ  ለመብቱና ለሕገ መንግሥቱ ዘብ እንዲቆም የሚያስችል እገዛ የሚያደርጉ፣ ከተለያየ ዓይነት የሙስና ተግባራትና ሕዝብን ከማጉላላት አሠራር የፀዱ፣ ሙስናንና የሥነ ምግባር መጓደልን የሚፀየፉ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚንቀሳቀሱ ይሆኑ ዘንድ አስፈላጊውን የሥራ ላይ ሥልጠናና ተከታታይ የረዥምና የአጭር ጊዜ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ሥልጠና ማመቻቸት የግድ ይላል። ከዚህ አንጻር ተከታታይ የአቅም ግንባታ ሥራ እንደሚሰራም እቅዱ  ዋና ጉዳይ አድርጎ አስፍሯል።

ለፍትህና ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ህዝብን ከማነቃነቅና ተሳትፎውን ከማጠናከር ጎን ለጎን አገራዊ መግባባትን መፍጠር ወሳኝ ነው። ህዝቡ በቀጥታም ሆነ በወኪሎቹ አማካይነት በአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በባለቤትነት ስሜት በንቃት መሳተፍ የሚችለው የተመቻቸ ሁኔታ ሲፈጠርለትና የፍትህና የመልካም አስተዳደር ማነቆዎች ሲወገዱ እንደሆነ እሙን ነው።

በተናጠልም ይሁን በተደራጀ መንገድ የፍትህ መጓደሎችን የሚተችና ገንቢ የማስተካከያ ሃሳቦችን የሚያቀርብበት ሥርዓት ያስፈልገዋል። ይህ የፍትህ ሴክተሩ እቅድ ካካተታቸው ዐበይት ተግባራት ዋናው ሆኗል።

ህዝቡ በተደራጀ መንገድ በቀጥታ የሚያደርገውን ተሳትፎ ውጤታማ ለማድረግ ግልጽ የተሳትፎ፣ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ሥርዓት ነድፎ ተግባራዊ የማድረግ አስፈላጊነት በመረዳት መንግሥት መስመሩን ከፍቶ በየደረጃ የመግባባት ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ይህ በቀጣይም ተጠናክሮ ይሰራል።

የህግ የበላይነትና የደህንነት ዋስትና መረጋገጥ ለፍትህ ሴክተሩ መጠናከር ሌላው ወሳኝ ነገር ነው። የፍትህና የጸጥታ አካላት ህዝቡን የመጠበቅ ተግባራቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉበት ይገባል። ንብረት የማፍራትና የመጠቀም መብቱን በተገቢው መንገድ ይጠቀምበት ዘንድ አስፈላጊውን ከለላ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ህገ ወጦችን ለሕግ በማቅረብ እርምት እንዲያገኙ ማድረግ ያሻል። ዜጎች በሠላምና በተረጋጋ ሁኔታ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ በማገዝ የፍትህና የመልካም አስተዳደር መረጋገጥ አካል ተደርጎ መወሰዱንም በእቅዱ ሰፍሯል።

ይህን ለመፈጸም የሚቻለው የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ ነው። ለዚህ ደግሞ የፍትህ ሥርዓቱ ነጻነቱ የተጠበቀ፣ ተቋማዊ ብቃት ያለው፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል የተደራጀና ለመላው ሕብረተሰብ ተደራሽ ሲሆን ነው። ይህ የፍትህ ሴክተሩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለመስራት ከተቃዱት ዐበይት ነገሮች አንዱ መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

የፍትህና የመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን እውን ለማድረግ፣ ሠላምንና ዲሞክራሲን ለማስፈን ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይታወቃል፡፡ ይህ ሲባል ልማትንና ዴሞክራሲን ለማጠናከር፣  ድህነትን ለመቀነስና ሠላምን ለማስፈን መሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ነው።

የፍትህና የመልካም አስተዳደር መስፈን ሕብረተሰቡ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ከአድልዎ የፀዳ ተጠያቂነትን የተላበሰ አገልግሎት እንዲያገኝ እገዛ ያደርጋል፡፡ በተለይ በአገራችን ከድህነት በፈጣን ሁኔታ ለመላቀቅ እየተካሄዱ ላሉ ትላልቅ አገራዊ ልማቶች የሚመደብ ገንዘብ የታሰበለት ዓላማ ላይ እንዲውል የፍትህ ዘርፉ የሚኖረው ሚና ቀላል አይደለም።

በፍትህ ሴክተሩ ያለው ማሕበረሰብ ለህግ  የበላይነት በቁርጠኝነት ሊቆም ይገባል። ህገ ወጥ ድርጊቶችን የሚከላከልና የሚቆጣጠር መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ የህግ የበላይነትን ለማስከበር የሚደረጉ ጥረቶች እንዳሉ የሚታወቅ ቢሆንም ተቋማዊና የሰው ኃይል አቅሙ አናሳ በመሆኑ ውጤት ለማምጣት አልቻለም።

ለህግ የበላይነት በቁርጠኝነት የቆመ የሥራ አመራርና ሙያተኛ መፍጠር፣ ህገ ወጥነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉና የሚያግዙ ተቋማት ማጠናከር፣ አሠራሮችንና ደንቦችን ፈትሾ ማስተካከልና ሙስና የሚፈጽሙትንና የሥነ ምግባር ችግር ያለባቸውን ግለሰቦች በፍጥነት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር ለፍትህ ሥርዓቱ መሻሻል ወሣኝ ሚና ስለሚኖረው በሃገር አቀፍ የፍትህ ሴክተሩ ቀጣይ እቅድ በሰፊው እንዲካተት ተደርጓል።

ግልጽነትን ለማስፈን፣ ተጠያቂነትን ለመተግበር፣ የሕዝብን ተሳትፎ ለማረጋገጥ፣ የኪራይ ሰብሳቢነት በርን ለመዝጋት መንግሥት የፍትህና የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ማዕቀፉን በመተግበር ላይ ይገኛል።  የፍትህ ሴክተሩ ችግሮች አለመቀረፍ ለአገሪቱ የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ እንቅፋት ከሚሆኑ መሰናክሎች መካከል ቀዳሚው መሆኑን ለሕብረተሰቡ በማሳወቅ በቀጣይ አጠናክሮ ለመተግበር መታቀዱን በፍትህ ሚኒስቴር የቀረበው ሰነድ ያሳያል።

በአገሪቱ ያለው የፍትህና የመልካም አሰተዳደር ችግር ለዘመናት የነበረና ሥር የሰደደ በመሆኑ ከስር መሠረቱ ለመቅረፍ ረዥም ጊዜ እንደሚጠይቅ በመገንዘብ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድን አውጥቶ ብልሹ አሠራርንና ሙስናን ትርጉም ባለው መልክ ለመቀነስ በሚያስችል መልክ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ በእቅዱ ላይ ሰፍሯል።

ፍትህን የማስፈንና መልካም አስተዳደርን የማረጋገጥ ጉዳይ ባለቤት ሳይኖረው በተበታተነ መልኩ ሊከናወን አይችልም። እቅዱ የሚሳካው ህዝቡ የሥራው ባለቤትነቱን አውቆ ሲንቀሳቀስ ነው። በየደረጃው ያለ አመራር፣ ሁሉም ሙያተኛና ባለድርሻ አካላት በጥምረት መስራት የሚያስችላቸውን ሁኔታ ሲፈጠር እንደሆነም ተመልክቷል።

በወንጀል መከላከል፥ በምርመራ በሕግ አወጣጥ፣ በፍርደኞች የይቅርታ አሰጣጥ፣ በሕግና ፍትህ ምርምር እንዲሁም በሰነዶች ማረጋገጫ በሚዘጋጁ እቅዶች፥ የእቅድ አፈጻጸሞችና ሪፖርቶች ላይ ህብረተሰቡን በንቃት ማሳተፍ አልተቻለም።

ከሕብረተሰቡ ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የውይይትና የግምገማ መድረክ ለማዘጋጀትና በቋሚነት ለመምራት ቁርጠኛነት እንዲኖርና የፍትህ አካላት ሕዝቡን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ የተለያዩ የሕዝብ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ትስስርን በማጠናከር አሳታፊነትን የማጎልበት እቅድም ተይዟል።

ዜጎች ለሚያነሱት ከፍትህ ዘርፉ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ጥያቄ ፈጣን ምላሽ አለመስጠትና አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ዜጎችን ጨዋነት የተላበሰና ሕጉ የሚፈቅደውን ቀልጣፋ አገልግሎት በክብር አለመስጠትን ለመቅረፍና የአገልጋይነት ስሜት አለመኖር፣ ውሣኔን በጊዜው አለማሳወቅ፣ ተገልጋዮችን ማመላለስና ሌሎች ከአመለካከት ችግር የሚመነጩ ችግሮችን ለማስወገድ የሚያስችል ሃሳብም በእቅዱ ተካቷል።

የቅሬታ ማስተናገጃ ማዕቀፎች በማዘጋጀት ዜጎች ቅሬታቸውን ማቅረብ የሚችሉበት አሠራር ለመፍጠርም ታስቧል። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የብዙኃን አደረጃጀቶችን በመጠቀም የግልጽነት አሠራሮችን በመዘርጋትና ለአመራሩና

ለፈጻሚው የአመለካከት መቃኛ የተለያዩ ሥልጠናዎችን ለመስጠት ቅድሚያ ተሰጥቶ ይከናወናል።

ለወንጀል መከላከል ሥርዓትን መዘርጋትና ክልሎችንም ያቀፈ ብሔራዊ የወንጀል መከላከል አቅጣጫ መከተል እንደሚያስፈልግና በዚህ ዙሪያ የተጀመረው ጥረትም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ሥልጠናዎችን መስጠት፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የታገዘ ምርመራ በማካሄድ በዘርፉ በሚታዩ ክፍተቶች የእርምት እርምጃ መስጠት እንደሚያስፈልግም ተለይቷል። የንቃተ ሕግ ትምህርትን ለህብረተሰቡ መስጠትም እንዲሁ።

ስለሆነም የሕግ የበላይነትን መርሆ በሚያስከብር መልኩ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቱን በማጥበቅ ለስኬት በሚያበቃ ሁኔታ ንቅናቄ ተፈጥሮ ይሰራል።

የዘርፉን አመራርና ባለሙያዎች አቅም በማሳደግ የዘርፉን እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በቀሪው ጊዜ ለማሳካት ርብርብ ይደረጋል። የማስፈጸም አቅም ማነስ ካጋጠሙ ፈተናዎች አንዱ በመሆኑ አጫጭር የሥራ ላይ ሥልጠናዎች በመስጠትና በየጊዜው ከህዝብ ጋር የሚደረገው የውይይት መድረክ ላይ የሚሰጡ ሃሳቦች በግብዓትነት በመጠቀም ለእቅዱ መሳካት ርብርብ እንደሚደረግ እቅዱ ያመላክታል።

የአገራችን ሁለንተናዊ ገጽታ እየተቀየረ መጥቷል። ይህ እኛ ብቻ ሳንሆን የዓለም ሕብረተሰብም እየመሰከረው ያለ ሃቅ ነው።

ይህንን እያደገ የመጣውን ኢኮኖሚ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ሁሉም ዜጋ በየደረጃው ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል መንገድ በመከተል ላይ እንዳለን የሚታወቅ ቢሆንም አሁንም በፍትህና መልካም ዘስተዳደር ሴክተር የልማቱን ያህል መፍጠን አልቻልንም።

አንድም በዘርፉ የሚሰሩ ባለሙያዎች ክህሎት ማሳደግ አስፈላጊውን ግብዓት ማቅረብና ሕብረተሰቡ የፍትህና የመልካም አስተዳደር መስፈን በዋናነት በራሱ ተሳትፎ የሚሳካ መሆነን አውቆ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ያስፈልጋል።